# *የለውጥ ፕሮግራሞች ፕሮጀክት ጥናትና ትግበራ ዋና የሥራ ሂደት*

## *የሥራ ሂደቱ ራዕይ /Vision/*

በ2010 ዓ/ም የተቀናጀ የማስፈፀም አቅም በመገንባት ድህነትንና ኋላ ቀርነትን በጽናት የሚዋጋ፣ ሁለንተናዊ የማስፈፀም አቅሙ የጐለበተ አሠራር ሲቪል ሰርቪስና የሲቪክ ማኅበራት ተፈጥሮ ማየት

## *የሥራ ሂደቱ ተልዕኮ /Mission/*

የአቅም ግንባታ የለውጥ ፕሮግራሞች ፕሮጀክት ፖሊሲዎች ፕሮግራሞችና ስትራቴጂዎችን በመተግበር በዞን በወረዳና በቀበሌያት ቀልጣፋና ውጤታማ ሲቪል ሰርቫንት መገንባት፣ የዳበረ የሥራ ባህልና ክህሎት ያለውን ሕ/ሰብ መፍጠር

## *የሥራ ሂደቱ ዓላማ/ Objectives/*

በአጭር ጊዜ ውስጥ ለተገልጋዮች ግልጽ ቀልጣፋና ውጤታማ አገልግሎት ለመስጠት ተደራሽ ግቦችን /ወጪንና ጊዜን ከጥራት ጋር/ ውጤታማ በሚሆኑበት መልኩ ለመጠቀም የሚያስችሉ ዘዴዎችን በመቀየስ መሠረታዊ ችግሮችን በመለየት መነሻና መድረሻን በመተለም እንዲሁም የጥናት ውጤቶችን ለውሣኔ አሰጣጥ ለመጠቀም የሥራ ቅደም ተከተልና ስታንዳርድ በመከተል ለውጥ እንዲመጣ ማድረግ ነው፡፡

## *የለውጥ ፕሮግራሞች ፕሮጀክት እሴቶች /Values/*

- የሕዝብ አገልጋይነት
- ብቃት
- ተነሣሽነት
- ግልፀኝነት
- ተጠያቂነት
- መልካም ሥነ ምግባር
- ለጋራ ራዕይና ተልዕኮ መስራት
- ቅንጅታዊ ሥራና ውጤታማነት
- አሣታፊነት
- በፆታ እኩልነት ማመን

- በለውጥ ማመን
- አካባቢን መንከባከብ
- ኤች አይ ቪ ኤድስን በጋራ መከላከል

## የለውጥ ኘሮግራሞች ኃላፊነትና ተግባራት

- የአሠራር ሂደት ለውጥ ትግበራ በዞንና በወረዳዎች እንዲተገበር ተከታታይ የአቅም ግንባታ ሥራዎችን /ግንዛቤና ሥልጠና/ ይሰጣል፣
- በለውጥ ኘሮግራሞች በዞንና በወረዳዎች የአጭርና የረጅም ጊዜያት እቅዶች ተነድፈው እንዲተገበሩ ግንዛቤና ድጋፍ ያደርጋል ይፈጽማል ያስተባበራል
- በመ/ቤቶችና በየሥራ ሂደቶች ውጠት ተኮር እቅድ አፈፃፀም በተደራሽ ግቦች / ጊዜ መጠን ጥራትና ወጪን/ አገናዝቦ መተግበሩን በድጋፋዊ ክትትል ያረጋግጣል ይደግፋል መረጃ ያሰባስባል፣ ያስተላልፋል፣
- በአገልግሎት አሰጣጥ መ/ቤቶች ለተገልጋይ የጊዜ ስታንዳርድና የእርካታ ምዘና በመለካት እንደሚያስተናግዱ ይከታተላል የምክር አገልግሎት ይሰጣል መረጃ ይሰበስባል
- የመ/ቤቶችንና የሥራ ሂደቶችን የቅሬታ አቀባበልና ምላሽ ስለሚሠራበት ሁኔታ ድጋፋዊ ክትትል ያደርጋል ለሚቀርቡትም ምላሽ ይሰጣል፣
- የገጠር ቀበሌያት ኢንስፔክሽን አገልግሎት በአፈፃፀም ደንቡ መሠረት መተግበሩን ይከታተላይ መረጃ ይሰበስባል፣
- ለቀበሌያትና ለወረዳ ሥራ አስኪያጆች፣ የኢንስፔክሽን አባላትና የቀበሌ አመራር በገጠር ልማት ፓኬጆች አፈፃፀም ግንዛቤ ይፈጥራል/ ውይይትና ሥልጠና/ ያካሄዳል
- የፍትህ ሥርዓት ማሻሻያ ኘሮግራም  በየደረጃው ባሉት መ/ቤቶች በቅንጅትና በተደራሽነት መተግበሩን ለድጋፋዊ ክትትል በተዘጋጀው ቼክ ሊስት ይከታተላል መረጃ ይሰበስባል፣
- የሂደደቱን የሕዝብ ግንኙነት ሥራዎች ያከናውናል፣
- የለውጥ ኘሮግራሞች አተገባበር የዳሰሳ ጥናት ያካሂዳል፣
-

## የሥራ ሂደቱ በተዛማጅነት የሚሠራባቸው መ/ቤቶች ተቋማት ድርጅቶች

- የዞንና የወረዳ የመንግስት መ/ቤቶች

- ኮሌጆች
- ሆስፒታል
- ጥቃቅንና አነስተኛ የንግድ ማኅበራት
- ት/ቤቶች
- የወጣቶችና የሴቶች ማኅበራት
- የክልል አቅም ግንባታ
- ሥራ አመራር ተቋም
- የሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ ወዘተ

## የሂደቱ ሌሎች ጠቃሚ መረጃዎች

- በሪፎርም ትግበራ የዳሰሳ ጥናት መረጃዎች
- የሪፎርም አፈፃፀም የዳሰሳ ጥናት ጽሁፎች
- ስለ አዲስ የአሠራር ሂደት ለውጥ ትግበራ የተሰበሰቡ መረጃዎች፣ የአፈፃፀም መመሪያዎች
- የቢፒአር የሥልጠና ማኑዋሎች
- በድጋፋዊ ክትትል የተሰበሰቡ መረጃዎችና ሪፖርቶች

## የሂደቱ የሰው ኃይል መረጃ

በአዲሱ የሥራ ሂደት ለውጥ ትግበራ የተፈቀዱ የሆኑ መምሪያ የለውጥ ኘሮግራሞች ኘሮጀክት ጥናትና ትግበራ ዋና የሥራ ሂደት ሲሆን የተፈቀደው 3 ባለሙያ ነው፡፡ ይህም አንድ አስተባባሪና ሁለት ፈፃሚዎችን የሚያካትት ነው፡፡ የሥራ መደቡ በርካታ የመምሪያውን ቁልፍ ተግባራት የሚተገበርበት ሆኖ በዲግሪና ከዚያ በላይ የት/ት ዝግጅት ይጠይቃል፡፡

